እንግዳው ኮከብ
በዶክተር መንግሥቱ ለማ

የመውለጃዋ ቀን የደረሰው እጮኛው የተቀመጠችበትን አህያ እየጎተተ ወደ ሰፈር ሲደርስ ከተማዋ የተወረረች ትመስል ነበር። በያቅጣጫው ባለው የከተማይቱ መግቢያ ወደ ውስጥ የሚጎርፈው ሕዝብ ብዛት ተጭኖ የሚነዳው አህያ ተለጉሞ የሚጎተተው ፈረስ ተሸልሞ የሚስጎትተው ሰረገላ ያችን ትንሽ መንደር አጨናንቋታል። ከገሊላ የመጣው የሰማርያ ዘመዱን ሲያገኝ፥ ከናዝሬት የመጣው ከቢታንያ የመጣውን አጥብቆ ሰላምታ ሲጠይቅ፥ ግፊያው፣ ጩኸቱና ትርምሱ ትንሿን ቤተልሔም የታላቂቱ የሮም ግዛት ዋና ከተማ አስመስሏታል።

"አገሩ ሁሉ ተገልብጦ እዚህ አይደለም እንዴት ያለው!?" አለ ዮሴፍ በመደነቅ ግራ ቀኙን እየቃኘ። ዮሴፍ በከተማው የሚያውቀው ሰው የለም። የትውልድ ሐረጉ ስቦ እዚህ ቢያመጣውም ዮሴፍ በዚህ አካባቢ ያሉትን ዘመዶቹን አያውቃቸውም። የመንግሥት ትዕዛዝ መጣስ ባይሆንበት ኖሮ ጊዜው ጨርሶ የጉዞ ጊዜ አልነበረም። ገና ከናዝሬት ሳይነሳ ይህን ሁሉ አስቦበታል። በአናጢነት ስራው ላይ ጎንበስ ቀና ሲል እንጨት ሲጠርብ ሳንቃ ሲገጥም አጠና ሲመትር ላለፉት ሁለት ሳምንታት ሲያስበው የሰነበተው የዚህን ጉዞ ሁኔታ ነበር።

አዎን ያ! እንግዳ ሰው በድንገት ተገልጦ "እጮኛህ ታረግዛለች።" ብሎ ምስጢሩ እስከዛሬ ድረስ በግልጽ ያልገባው እንቆቅልሽ ነግሮት ከሄደ ዘጠኝ ወር ሊገባደድ ነው።

ዘጠኝ ወር ሙሉ ደብቆ የያዘው ይህ እንቆቅልሽ ምንድንነው? (ማቴዎስ 1፤ 18-23)

ዮሴፍ ጉዞውን ሲጀምር የነበረው የተስፋ ጭላንጭል የመውለጃዋ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ደርሰን እንመጣለን የሚል ነበር። ግና፤ መንገዱን ከጀመሩት በኋላ የወጣት እጮኛው መድከም የፊትዋ መንጠልጠል የእግሯ መከባበድ ይህንን ተስፋውን አጨልሞበታል። በልጅነት አቅምዋ ጨክና ይዛው ነው እንጂ፥ በተለይ ባለፉት ሁለት ቀናት በጣም መድከሟን ተረድቶታል።

ዮሴፍ ቤተልሔም ሲደርስ ከሁሉ አስቀድሞ ሊያደርግ የወሰነው ለተዳከመችው እጮኛው የማረፊያ ቦታ መፈለግ ነበር። የከተማዋን መተረማመስ ሲያይ ግን ስጋት ገባው። የማደሪያ ቦታዎች በሙሉ ቀድመው መያዛቸውን አወቀ። ሲፈራ ሲቸር ወደ አንድ የማደሪያ ስፍራ ገብቶ ጠየቀ። እንደሞኝ ተመለከቱት። "ነፍሰ ጡር ሴት ይዣለሁ መውለጃዋ የተቀረበ ይመስለኛል።" አለው ሁለተኛ የቆበመትን የማረፊያ ቦታ አከራይ። "ትዕዛዙን እንዲሽር ለአውግስጦስ ቄሳር አቤት ብትል ሳይሻል አይቀርም።" ብሎ አሾፈበት። (ገበያው የሞላለት ነጋዴ በሌላ ጊዜ ደንበኛ የሚፈልግ አይመስለውም።) ዮሴፍ ግን ተስፋ ባለመቁረጥ ከአንዱ ማደሪያ ወደ ሌላው እየሮጠ ቢማጸን፣ ቢለማመጥና ቢለምንም አልሆነለትም። በአንድ መንገድ ጥግ ከዕቃው ጋር ተቀምጣ በአይንዋ የምትከተለው እጮኛው ማርያምም ከድካሟና ከህመሟ ጋር የዮሴፍን ከወዲያ ወዲህ መንከራተት የምትመለከተው በሃዘኔታ ነበር።

ማርያም ዘመድዋን ኤልሳቤጥን ለመጠየቅ ወደ ደጋው አገር ወጥታ ከተመለሰች ወዲህ ራቅ ወዳለ ቦታ ስትሄድ ይህ የመጀመሪያ ጊዜዋ በመሆኑ ብዙው ነገር እንግዳ ሆኖባታል። ትርምሱ፣ ግፊያው፣ ሁካታው የሁሉ ነገር መቻኮል አስደንቋታል። ሆኖም በልብዋ ጠብቃ የያዘችው ያ ትልቅ ምስጢርና በማህጸንዋ ተረግዞ ያለው ህጻን ከዚህ ሁሉ ግርግርና ረብሻ በላይ የሆነ የመንፈስ እርካታ ስለሰጣት፤ በሁኔታው አልተናደደችም። በድካምዋም አላጉረመረመችም።

ለመሆኑ በልብዋ የያዘችው ይህ ታላቅ ምስጢር ምን ይሆን? (ሉቃስ 1፤26-35)

የዮሴፍ ትሕትናና ከመንገድ ዳር ቁጭ ያለችው ወጣት ሁኔታ ልቡን የነካው አንድ የመጠለያ ስፍራ አከራይ ወደ ዮሴፍ ጠጋ ብሎ፥ "የተሻለ ማረፊያ ቢኖረኝ ኖሮ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ ላላችሁ ወገኖቼ በነፃም ባሳርፋችሁ ደስ ባለኝ ነበር።" አለው። ዮሴፍም፥ "ማረፊያ እስከሆነ ድረስ ተሻለ አልተሻለ ለመምረጥ የምንችልበት ሁኔታ ላይ አይደለንም።" አለው። ቀጠል አድርጎም፥ "ይህች ሴት መውለጃዋ ከደረሰ ሰንብቷል። እንዲያውም መንገድ ላይ ጉድ እሆናለሁ ብዬ በጣም ሰግቼ ነበር። የአባታችን የዳዊት አምላክ ግን እዚህ እንድንደርስ አደረገ። አሁንም ከመንገድ ላይ ብቻ ተነስታ ዞር የምትልበትን ስፍራ ነው የምፈልገው።" አለው።

ሰውየውም እየሰጋ፥ "ከብቶች የሚያድሩበት ትልቅ ግርግም አለኝ። ሰፋ ያለ ስለሆነ ከአንድ ወገን ከጎዘጎዝኩላችሁ ከመንገድ ዳር በጣም ሳይሻል አይቀርም።" አለው። "ያልከኝን እከፍላለሁ።" አለው ዮሴፍ። መልሶም ከሰውየው አፍ ነጠቀና፥ "የአብርሃም አምላክ ውለታህን ይክፈለው።" አለው። ሰውየው ኪራይ አልፈለገም። የበረቱን አንደኛውን ስፍራ ለየት አድርጎ ክልል ለመሥራትና ጎዝጉዞ ነፍስ ጡሯን ለማስተኛት ለአናጢው ለዮሴፍ ምንም ጊዜ አልወሰደበትም።

ማርያምን ካስተኛ በኋላ ግርግሙ በር ላይ ተቀምጦ የጀምበሯን መጥለቅ እየተመለከተ ቀኑን እንዴት እንዳሳለፈው ለማሰላሰል ቢሞክር በጣም ረጅም ቀን እንደነበረ ታወሰው። የእጮኛውን የማርያምን ሁኔታ ሲመለከት ደግሞ ከዘጠኝ ወር በፊት መጥቶ የጎበኘው ያ እንግዳ ሰው እንደገና ትዝ አለው። እንግዳው ያካፈለውን ምስጢር ሲያሰላስል ደግሞ ከዚህ በፊት የማያውቀው አይነት ደስታ ቀስ እያለ ሰውነቱን ወረረው። ከጥቂት ጊዜ በፊት የደረሰበትን መሯሯጥ፣ ግልምጫና ተስፋ መቁረጥ የሚያስረሳ ሰላም ሰፈነ።

የቤተ ልሔም በረት ለእኛ ደስታ ነው ?

በፀሐይዋ መጥለቅ ቀይ የነበረው ሰማይ እየጨለመ መጥቶ ከዋክብት መፈነጣጠቅ ጀመሩ። በጉዞ ላይ የዋለውን ሰውነቱን ለማሳረፍ ሲዘጋጅ ነበር ከወደ ምሥራቅ ያንን እንግዳ ኮከብ ሲመጣ የያው። ኮከቡ ከሌሎች ከዋክብት ለየት ያለ ነበር። ቀስ ብሎ ይጓዛል። በጣም ደማቅ ነው። እንግዳ ኮከብ መሆኑ በእርግጥ ያስታውቃል፤ ዮሴፍ ግን በኮከቡና በእርሱ መካከል አንድ ምስጢር እንዳለ ተረዳ። ለሌሎች እንግዳ ቢመስልም፥ ስለከዋክብት ምንም ነገር ለማያውቀው ለዮሴፍ ግን ይህ ኮከብ እንግዳ አልሆነበትም። ጭራሽ የኮከቡ መገለጥ የበለጠ ደስታ ሰጠው። አተኩሮ ሲመለከት ቀስ እያለ ወዲህ እንደሚመጣ አስተዋለ። ብርሃኑም እርሱ ባለበት ቦታ ላይ ያተኮረ መሰለው።

በመጨረሻ ብድግ ብሎ “ተመስገን አምላኬ በሰላም ዛሬ እዚህ ያደረስከን …” አለና “እንግዲህ ነገም ሌላ ቀን ነው።” ማለት ሲጀምር ራሱን ተጠራጠረ። በውስጡ ነገ ሌላ ቀን ብቻ አልመሰል አለው፡፡ በሚቀጥለው ቀን የዓለም ታሪክ መለወጡን ባይገነዘብም በራሱ ውስጥ የሚካሄድ የለውጥ እንቅስቃሴ መኖሩ ግን ተሰማው፡፡”ሕጻኑ … ዛሬ ይሆን እንዴ?” ብሎ ራሱን ጠየቀና ወደ ግርግሙ ገባ፡፡

እረኞች ከብቶቻቸውን እየጠበቁ በሜዳ ማደራቸው በቤተልሔም ወረዳ የተለመደ ነገር ነው፡፡ እንዲያውም ተረት ሲተርቱ፣ እንቆቅልሽ ምን አውቅልሽ ሲጠያየቁ፣ ሲቃለዱና ሲሳሳቁ ሰለሚያመሹ ብዙዎቹ ሜዳ ማደርን ይወዱታል፡፡ ለምለም እሸት ካለ ሸምጥጠው ሲጠረጥሩ ያመሻሉ፡፡ እሸቱ ደረቅ ካለም ቆሎውና ንፍሮው ይዘጋጃል፡፡ ሰማዩ ጥርት ያለ እንደሆን ደግሞ ሽቅብ ወደ ሰማይ እየተመለከቱ ኮከብ ሲቆጥሩ ያመሻሉ፡፡

ዛሬ ግን ይቺን ትንሽ ከተማቸውን እንግዶች ሙልት ስላደረጓት የእረኞቹ ወሬ በእንግዶቹ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ አንዱ ከቃና የመጣው ሃብታም ስላስከተለው አጀብ ሲያወራ ሌላው ደግሞ ከደማስቆ የመጣው ባለሥልጣን ስለሚያስጎተተው ሠረገላ ይናገራል፡፡ ከገሊላ የመጣው አሳ አጥማጅ ከርፋፋነት ከግብጽ የመጣው ነጋዴ አነጋገር … ይህ ሁሉ የዚህ ምሽት ወሪያቸው ነበር፤ ልብ ያላሉት ግን ከናዝሬት የመጣው አናጢ ወረግቡ እጮኛውን በረት ማስተኛቱን ነበር፡፡ እረኞቹ እንደልማዳቸው ያነደዱትን እሳት ከበው ሲያወኩ ካመሹ በኋላ በየቡድናቸው ተበታትነው የመጀመሪያው ዙር ጠባቂ ወደ መጠበቂያው ስፍራ ሲሄድ ሌሎቹ ባሉበት ቦታ ጋደም ጋደም አሉ፡፡

ዘካርያስ ከብዙዎች እረኞች በዕድሜ ገፋ ያለ ቢሆንም ብዙ ጊዜ የመጀመሪያውን ዙር ጥበቃ ይወደዋል፡፡ ዘካርያስ በተፈጥሮው የከዋክብትን አቀማመጥ ድምቀትና አካሄድ አተኩሮ ማየት ሰለሚወድ ኮከቦቹ ሳይከስሙ ብሎ ነው የመጀመሪያውን ዙር የሚጠብቀው ብዙ ጊዜ ደግሞ በከዋክብት ሁኔታ ያለፈውንና የሚመጣውን ስለሚናገር በሌሎች እረኞች ዘንድ “ኮከብ ቆጣሪው” የሚል የቅጽል ስም አትርፏል፡፡

ከዋክብት ደስ ይሉታል፡፡ ከዋክብት ያፈላስፉታል፤ ያዝናኑታል፡፡ እንደ ጸሐይ ብቸኛ የሆኑት ያሳዝኑታል፡፡ በርከት ብለው በአንድነት ያሉት ለሐሜት የተሰበሰቡ እየመሰሉት ያስቀኑታል፡፡ በሚከተሉትም ሥነሥርዓት ያስገርሙታል፡፡ አንዱ ብልጭ ሲል ወዲያው ሌላው ጥፍት ስለሚል እርስ በርሳቸው ድብብቆሽ የሚጫወቱ እየመሰለው አንዱ ሳይበራ ሌላው የሚጠፋበትን ጊዜ በጉጉት ይጠብቃል፡፡ አንዱ ኮከብ በሌላው ዙሪያ ሲሽከረከር ያየ እንደሆን ልጅነታቸውን ያልጨረሱ ገና “አዙረኝ - አታዙረኝ” የሚጫወቱ እየመሰለው ያስቁታል፡፡ አንዳንዶቹ ተጠጋግተው እስከመሳሳም ሲደርሱ ፍቅረኞች እየመሰሉት የጉርምስናውን ዘመን ያስታውሱታል፡፡ ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ከሄዱ ደግሞ የተኳረፉ እየመሰለው ይታዘባቸዋል፡፡ ተፋጠው ሁልጊዜ የሚተያዩት ግን አሸናፊው ገና ያልለየ “እስቲ ንካኝ - እስቲ ንካኝ” የሚባባሉ ስለሚመስለው ልቡን ሰቅል ያደርጉታል፡፡ ለየትኛው እንደሚያግዝም ግራ ይገባዋል፡፡ ብርሃናቸው በጣም ደማቅ ከመሆኑ የተነሳ ለሌሎችም የሚተርፉትን ሰማያትን ለማጌጥ የተፈጠሩ እንቁዎች ስለሚመስሉት እንደብርቅ ያያቸዋል፡፡ ከደብዛዛነታቸው የተነሳ በደንብ የማይታዩት ደግሞ ያላቸውን የማይለግሱ ስስታሞች ሆነው ስለሚታዩት ከልቡ ይንቃቸዋል፡፡ ባለማቋረጥ የሚያበሩ ከዋክብት አሉ፡፡ ለተወሰነ ጊዜ በርተው የሚጠፉ እንደገና ጊዜያቸውን ጠብቀው የሚበሩ አሉ፡፡ ብርሃናቸው እንዳያልቅባቸው የሚቆጥቡ ይመስሉታል፡፡ ለማብራት ወይም ላለማብራት ያልወሰኑ እንዲያው መካከል ቤት ደም መስለው የሚኖሩት ገና እንቅልፋቸውን ያልጨረሱ ስለሚመስለው የሚነቁበትን ጊዜ በጉጉት ይጠብቃል፡፡ ሞገስ ባለው ሥነ ሥርዓት የሚጓዙ ቅጥ ባጣ ሁኔታ እየተቅበዘበዙ የሌሎችንም ሥርዓት የሚረብሹ ከዚያ ተተኩሰው መጥተው እዚህ የሚለኮሱ ነካ ያደርጋቸው ይመስል የቆሙበት ቦታ እንደ እንዝርት የሚሽከረከሩ … ከዋክብት ብዙ ናቸው፡፡ ዘካርያስም እነርሱን ሲያይ ብዙ ጊዜ ያጠፋል፡፡

ዛሬም እንደ ልማዱ ከመጠበቂያው ላይ በጀርባው ተንጋሎ በጠራችው የይሁዳ ሰማይ ላይ የተበታተኑትን ከዋክብት ማጥናት ጀመረ፡፡ ዘካርያስ ከዋክብትን የሚያጠናው ለመዝናናትና ለመፈላሰፍ ብቻ አልነበረም፡፡ ከዋክብትን ሲያይ ሲመራመር ከከዋክብት በላይ ያለው የአባቱ የዳዊት አምላክ ቀረብ ስለሚለውም ነው፡፡ እነኚህን ሁሉ ከዋክብት ከርክሞና አስተካክሎ የሠራው አምላኩ ቀረብ ሲለው ደግሞ ልቡ በደስታ አፉ በምሥጋና ይሞላና አዲስ የሕይወት እስትንፋስ በውስጡ ማንሰራራት ይጀምራል፡፡ ዛሬም ልክ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ እንዳለ ነው ድንገት ያንን እንግዳ ኮከብ ከወደ ምሥራቅ ሲመጣ ያየው፡፡ የተለየ ምስጢር የያዘ ኮከብ መሆኑ ለሽማግሌው ለዘካርያስ ግልፅ ነበር፡፡ ኮከቡ እየቀረበ በመጣ መጠን የዘካርያስ የልብ ትርታም እየጨመረ፣ ምስጋናው ከፍ እያለ፣ ደስታውም እየላቀ የሕይወቱም መታደስ እየበራ መጣ፡፡ ኮከቡ በጣም እየቀረበ መጥቶ ከቤተልሔም ከተማ ትይዩ ሲሆን ቀጥ ብሎ ቆመ፡፡ እረኛው ዘካርያስ በደስታ ተሞልቶ ሲያመሰግን ተኝተው የነበሩት ጓደኞቹ ተደናግጠው ተነሱ፡፡ ለመቆም እየተጣደፉ ሳሉ ታላቅ የብርሃን ነጸብራቅ በዙሪያቸው ሆነ፡፡ ከብርሃኑ ኃይል የተነሳ መቆም አቅቷቸው ሲርበደበዱ፥ ብርሃን ለብሶ ብርሃን ተጎናጽፎ አንድ መልእክተኛ ተገለጠ፡፡ መልአኩም እንዲህ አላቸው።

“ለሕዝብ ሁሉ የሚሆን ታላቅ የምሥራችን እነግራችኋለሁና አትፍሩ አላቸው፡፡ ሉቃ 2፥10-12

ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ፡፡ አቤት! እረኞቹ እንዲህ ያለ ነገር አይተውም ስምተውም አያውቁም፡፡ የፍጥረታት ሁሉ እንቅስቃሴ የሠራዊቱ ውዝዋዜ የመላእክት ሽብሽባ ይህ ነው ተብሎ የማይነገር የሙዚቃ ቃና አስተጋባ፡፡ የዱዳን ልሳን ፈትቶ የሚያዘምር ደስታ፤ ሽባን ተርትሮ የሚያስጨፍር ሁኔታ፤ ከዋክብት ሁሉ አብረዋቸው የሚጨፍሩ፤ ጨረቃ ልብዋ እስኪወልቅ እስክስታ የምትወርድ መሰላቸው፡፡ ነፋሱ የሰላም ሽውታ፤ አጽዋቱ የፍቅር መዓዛ፤ የወንዙና የፏፏቴው ድምጽ የደስታ የምሥራች አስተጋባ፡፡ ሰማይ ከመጠን በላይ ደመቀ፤ አሸበረቀ፤ ምድርም አጀብ አለች፡፡

ደስ ይበለን ደስ ይበልን እንዘምር በደስታ
መቸገራችንን አይቶ ወረደልን ጌታ…

ብዙ አልቆዩም መልእክተኞቹ ተመልሰው ወደመጡበት ሄዱ፡፡ “የእግዚአብሔርን ክብር በዓይኖቻችን አይተናል በጆሮአችንም ሰምተናል፤ ታዲያ እንዲህ ያለውን ታላቅ የምሥራች ይዘን እንዴት አስችሎን ዝም እንላለን፡፡” አለ ሽማግሌው ዘካርያስ፡፡ በአባቶቹ በነቢያት የተተነበየለትን ለብዙ ዘመናት የተጠበቀውን መሲህ ለማየት ዓይኖቹ እየናፈቁ፡፡ የሽማግሌ ወገቡን የሚደግፍበትን ምርኩዙን አንስቶ ባለው ፍጥነት ሁሉ ቤተልሔም ውስጥ ወዳለችው ወደዚያች በረት ሮጠ፡፡ ሌሎቹም እረኞች ምስጢሩ ሙሉ በሙሉ ባይገባቸውም ተነስተው ዘካርያስን ተከተሉት፡፡ ዘካርያስ ከእንግዲህ ቤተልሔም ትንሽ መንደር ብቻ እንዳልሆነች ተረዳ፡፡ ከእንግዲህ

ይሁዳን ብዙ ሰዎች እንደሚያውቋት ገባው፡፡ ከእንግዲህ ዓለም ታሪኳ እንደተለወጠ ተገለጸለት፡፡ ያልተመለሰለት ጥያቄ ግን ሕዝቡን ነፃ የሚያወጣውና እስራኤልን የሚሰበስበው ንጉሥ በበበረት መወለዱ ነበር፡፡ ሆኖም የምሥራቹን ቃል ከመናገር ወደ ኋላ አላለም፡፡

የምሥራቹ ቃል በድንገት ተሰማ
በከብቶች በረት ውስጥ ቤትልሔም ከተማ
ምንም ቢዘገይም ቢታይም ርቆ
ኢየሱስ ተወለደ ጊዜውን ጠብቆ ...

ዝቅ ብሎ ከደቡባዊ ምሥራቅ ጀምሮ፣ ኤዶማውያንን ይዞ፣ ሞአባውያንን ይዞ፣ አሞናውያንን ይዞ፣ አረማውያንን ይዞ፣ ሰሜን ምስራቅ ጫፍ ያሉትን አሦራውያንን ጨምሮ ራቅ ብሎ እስከ ፋርሳውያን ደረሰ፡፡ ይህ ሕዝብ የምሥራቅ ህዝብ በመባል ይታወቃል፡፡ በይሁዳ አካባቢ ደግሞ የምሥራቅ ሕዝብ ማለት ጥበበኛ ማለት ነው፡፡ በተለይ ፋርሳውያንና ምድያውያን፥ ሕልም በመፍታት፣ ራዕይ በመተርጎም፣ በመጠንቆልና በኮከብ ቆጠራ ዝናቸው የገነነ ስለነበር እንኳን ዛሬ የይሁዳ መንግሥት ወድቃ በአህዛብ በተገዛችበት ጊዜ ቀርቶ ድሮም በኃይለኛ መሳፍንቶችዋና ነገሥታቷ ጊዜ የምሥራቅን ጥበብ ዝቅ አድርጎ የሚመለከት መሪ አልነበራትም። ስለከዋክብትም ቢሆን የምሥራቅ ሰዎች ያላቸው አስተሳሰብ ከይሁዳ እረኞች በጣም የመጠቀና የረቀቀ ነው፡፡

የከዋክብትን መልክ አይተው ዕድሜያቸውን ይናገራሉ፡፡ በዚህም የጠቅላላውን ሥነ ፍጥረት አመጣጥ ለማብራራት ይሞክራሉ፡፡ ሰማያዊ ከዋክብት ገና ወጣት ስለሆኑ አፍላቸውን ያልጨረሱ ናቸው ይላሉ፡፡ ቢጫ ከዋክብት ግን መካከለኛ ዕድሜ ላይ የደረሱ ስለሆኑ ረጋ ያሉ ናቸው ይላሉ፡፡ ቀያይ ከዋክብት ያረጁና ሊጠፉ የተቃረቡ ሲሆኑ ከዋክብት ከጠቆሩ ወይም ከነጡ መሞት ጀምረዋል ማለት ነው ይላሉ፡፡ ደማቅ ብርሃን ያላቸው ከዋክብት ቀረብ ያሉ መሆናቸውን ትንንሽ መስለው የሚታዩት ደግሞ በሩቅ የሚኖሩ ትላልቅ ከዋክብት መሆናቸውን በጥናታቸው ያመለክታሉ፡፡ ይህንንም ተመርኩዘው የሳዋን አቀማመጥና የመሬትን ዕድሜ ይተምናሉ፡፡ ከዋክብት ልክ እንደሰው ዘር ዜግነት ያላቸው አመጣጣቸውና አቀማመጣቸው ከዜግነታቸው ጋር የተዛመደ መሆኑን ያስረዱና የከዋክብት ሥርዓት ከተናጋ የመዓት ዘመን እንደሚመጣ ስለሚያውቁ አስቀድመው ያስጠነቅቃሉ፡፡ የምሥራቅ ጠቢባን ሲያስጠነቅቁ ደግሞ እንደቀልድ የሚወስደው ማንም የለም፡፡

ሆኖም ይህ እንግዳ ኮከብ መጥቶ በደማቅ ብርሃኑ ከሌሎች ተለይቶ በሥርዓቱ የተፈጥሮን ሕግ አፍርሶ ሲያዩት እንደሌላው ጊዜ አልተደናገጡም፡፡ ለሕዝቡም ማስጠንቀቂያ ለመስጠት አልሞከሩም፡፡ ሊያጠኑት ቢሞክሩ ከዕውቀታቸው ሁሉ በላይ የሆነ ምስጢር የያዘ ኮከብ መሆኑን ተገነዘቡ፡፡ ችላ ብለው እንዳይተውት ኮከቡ ችላ የማይባል መልዕክት ይዞ እንደመጣ ገባቸው፡፡

በመጽሐፍ ይሁዳን ሰብስቦ የተጠናከረ መንግሥት አቋቁሞ የሚገዛ ንጉሥ እንደሚነሳ አንብበዋል፡፡ ይህ ተስፋ ለእስራኤል በመሆኑ ጠንካራ የጎረቤት መንግሥት ይነሳብናል ብለው ይሰጉ ነበር፡፡ በመጽሐፍ የተጻፈ ተስፋ ሁሉ ለእስራኤል ልጆች ብቻ ስለሆነ የዚህ ዕድል ተካፋይነት እንደሌላቸው ዘወትር ይናገራሉ፡፡ ሆኖም ያ እንግዳ ኮከብ መጥቶ በሁኔታው ሁሉ ከሌሎች ተለይቶ ሲያዩት ለእነርሱም የሚሆን ተስፋ እንዳለው ተረዱ፡፡ የሚያስፈራ ኃይለኛና ጠንካራ የጎረቤት ንጉሥ መወለዱን ሳይሆን ለብዙዎች የሚራራ የሰላም አለቃ መመወጣቱ ተሰማቸው፡፡ የሚጠሏቸውንና የሚፈሯቸውን እስራኤላውያንን ይሰበስባል የተባለው ይህ ንጉሥ የቀደሙ አባቶቻቸውን እንዳሸነፈው እንደ ሙሴ የማይበገር ፖለቲከኛ ብቻ ሆኖ አልታያቸውም፡፡ ወይም ጦራቸውን ሁሉ በድል እንደፈታው እንደ ኢያሱ ግንባሩን የማያጥፍ የጦር መሪ ብቻም አልመሰላቸውም፡፡ በታላቁ ጥበባቸው ተመራምረው ሊደርሱበት ባይችሉም ይህ ኮከብ የምሥራች ይዞ እንደመጣ ታውቃቸው፡፡ ይህ ኮከብ ወደ ተስፋ እንደሚመራቸው አስተዋሉ፡፡ ምስጢሩን ለመመርመር ጊዜ አልፈጁም፡፡ ሳያውቁት ለናፈቁት ለዚህ አዲስ ሕጻን የሚሆን ሽልማታቸውን ጭነው የእንግዳውን ኮከብ መሪነት ተማምነው ወደ ምዕራብ ጉዞ ጀመሩ፡፡

ታላቁ ሄሮድስ በዲፕሎማሲ ጥበቡ በጣም የተደነቀ ሰው ነበር፡፡ ባንድ በኩል ለታላቂቱ ሮማ ቄሳር ያለበትን ኃላፊነት ሳያዛባ በሌላ በኩል የሚገዛውን የይሁዳን ሕዝብ መሪዎችንም ሳያጉላላ ከሁለቱም በኩል ያለውን ሚዛን ጠብቆ በማስተዳደሩ "ታላቅ" የመባልን ዝና አትርፏል፡፡ እንዲያውም በሠላሳ አምስት ዓመተ ዓለም ገደማ በሮማ በተደረገው የመንግሥት ብጥበጣ ጁሊየስ ቄሳር ተገድሎ አውግስጦስ ቄሳር ሲነግስ ብዙዎቹ የሮማ ቅኝ ግዛት አስተዳዳሪዎች በተሻሩበት ጊዜ ታላቁ ሄሮድስ ካስተዳዳሪነት ጭራሽ ወደ ንጉሥነት በመሾሙ በፖለቲካ ብስለቱና በዲፕሎማሲ ስትራተጂው ለሮማ አስፈላጊ መሆኑ ተመስክሮለታል፡፡ በኢየሩሳሌም ደግሞ የፈረሰውን የሰለሞንን ቤተ መቅደስ በማሰራቱ የአይሁድን ካህናት ወዳጅነት አትርፎአል፡፡ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ደግሞ ካህናት የራሳቸውን የሆነ የቀረጥ ሰርዓት እንዲኖራቸው በመፍቀዱ በቤተ መቅደሱ ስምም የተለያዩ ንግዶች እንዲያከናውኑ በማድረጉ የይሁዳ ካህናትን ስሜት ግዝቶ ነበር፡፡ ስልጣኑ እዚህ ደረጃ ላይ ደርሶ ለዕድገቱ ምንም መጠን እንዳማይኖረው በሚያውጠነጥነበት በዚህ ጊዜ ነበር ይህ ያልጠበቀው ወሬ መንፈስ የጀመረው፡፡

"የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው ያለው? ኮከቡን አይተን ልንሰግድለት መጥተናል፡፡" የሚሉ የምሥራቅ ጠቢባን ኢየሩሳሌም ደርሰዋል ብለው ነገሩት፡፡ በአስተዳዳሪነትና በንጉሥነት ከአርባ ዓመት በላይ የቆየ በመሆኑ ወሬው በመጀመሪያ አላስደነገጠውም፡፡ ቀስ ብሎ ግን ከነከነው፡፡ አይሁዶች ምንም ቢወዳቸው ልባቸውን ከፍተው እንዳልተቀበሉት ያውቃል፡፡ በየምኩራባቸው በየጊዜው "እስራኤል ትሰበሰባለች ይሁዳም ነጻ ትሆናለች።" የሚል ስብከት እንደሚሰበክ ሰምቷል፡፡ ፊታቸውን ባስተዋለ ቁጥር ትምክሕትና ተስፋ እንደሞላባቸው ያያል፡፡ "የማይጠፋ ዘር ነን።" ይላሉ፡፡ "ለእግዚአብሔር የተለየ ወገን ነን ... " ይላሉ። ከሌሎች መቀላቀልን እንደማይወዱ ያውቃል፡፡ ቀስ በቀስ እርሱ ያልደረሰበት ምስጢር ከእርሱ የተደበቀ ዕውቀት መኖሩን ተገነዘበ፡፡ ቁጣው በጣም ነደደ፡፡ ብስጭቱ በዙፋኑ ላይ አቁነጠነጠው፡፡ ሆኖም ስትራተጂ አዋቂ ነውና ቁጣውን ዋጥ አድርጎ ከነገሩ ስር ለመድረስ ወሰነ፡፡ የቅርብ ወዳጆቹ የሆኑትን ካህናት አሰጠርቶ "ንጉሣችሁ የሚወለደው ወዴት ነው።" ብሎ ጠየቃቸው፡፡ የነቢዩን የሚክያስን ቃል አነበቡለት፡፡ (ሚክያስ 5፤2-4)

ሄሮድስ ይህን ሲሰማ በውስጡ የማያወላውል ውሳኔ አደረገ፡፡ "መንግሥቴን የሚቀናቀን ሁሉ ይጠፋል።" ሲል አተመ፡፡ ከማን ጋር እንደሚዋጋ ግን በግልጽ አላወቀም፡፡ በታላቂቱ የሮማ ጦር ሠራዊት ውስጥ የሰለጠኑትን ወታደሮቹን ሊቋቋም የሚችል ማንም እንደሌለ በትምክህት አሰበ፡፡ ከምክንያት ሁሉ በላይ የሆነ ፍርሃትና ጭንቀት ስለያዘው "ገና ሳያድግ ከአሁኑ መቅጨት ነው።" አለ፡፡

ጠቢባኑን አስጠርቶ “ሂዱና ስለተወለደው ሕጻን በጥንቃቄ መርምሩ፤ ... እኔም ደግሞ እንድሰግድለት መጥታችሁ ንገሩኝ።” አላቸው።። እንደ ልማዱ ሌላ የዲፐሎማሲ ሸፍጥ የፈጸመ መስሎት በትምክህት ተዝናና።።

ጠቢባኑ ሕጻኑን መጥተው ባዩት ጊዜ ሞገስ የሞላበት መሆኑን አስተዋሉ።። ወድቀውም ሰገዱለት።። ገጸ በረከትም አቀረቡለት። ስጦታውን ሲያመጡ ግን አሳባቸው ተመሰቃቀለባቸው።። ንጉሥ ነው ብለው ስላመኑ እንደ ንጉሥነቱ ወርቅ ሰጡት።። ግን ንጉሥ ብቻ እንዳልሆነ ተረዱ።። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ የሚያስታርቅ ታላቅ ሊቀ ካህን ሆኖ ስለታያቸው ለክህነት ስራው የሚውል ዕጣን አቀረቡለት።። ያም ሆኖ ልባቸው አልደረሰም።። ከርቤ በአይሁድ ባህል አስከሬን የሚገነዘበት ስለሆነ ገና ለሚያድግ ሕጻን ስጦታ አድርጎ ማቅረብ ስሜት እንደማይሰጥ የምስራቅ ጠቢባን አሳምረው ያውቃሉ።። እስከዛሬ ድረስም እንደዚህ ያለ ድፍረት ሞክረው አያውቁም።። ዛሬ ግን ያንን ዕውቀታቸውን የሚደመስስ ታላቁን ጥበባቸውን የሚያስንቅ ሊገልጡትና ሊያስረዱት የማይችሉት ሌላ የበላይ የሆነ ኃይል ግድ ስላላቸው አዲስ ለተወለደው ሕጻን ወርቅም ዕጣንም ከርቤም ገፀ በረከት አድርገው ሰጡት።።

ህጻን ተወልዶአል በቤተልሔም

በአካባቢያቸው ያሉት ሁሉ ግራ በመጋባት ይመለከቷቸው ነበር።። የሕጻኑ በበረት መወለድ አስደንቋቸው ሳያበቃ እነኚህ ጠቢባን ነን ባዮች ደግሞ የሚያደርጉት የበለጠ አስረገማቸው።። ነገሩ ሁሉ በጣም እንግዳ ሆነባቸው።። ቀደም ሲል ከዱር የመጡ እረኞች “መድኃኒት መወለዱን ሌሊት መላዕክት መጥተው አበሰሩን።።” ብለው ነግረዋቸው ነበር።። አላመኗቸውም።። ግማሾቹም “መቼም እረኞች ናቸውና ምናልባት የግብፅ ነጋዴዎች ሲያልፉ አታለዋቸው ነው።።” ብለው ናቅ አድርገዋቸዋል።። ሌሎቹ ግን እነኚህ በጥበባቸው ዓለም ሁሉ ያደነቃቸው አሕዛብ ይህን የሚያክል የሞኝነት ሥራ ሲሠሩ በማየታቸው ሳቁባቸው።። አሟቸው። ሆኖም መደነቃቸው አየለ።። ሕጻኑን ታቅፋ ጋደም ያለችው አራስ በሆድዋ ጠብቃ የያዘችው ምስጢር ምን መሆኑን እንኳን ያወቀ የለም።። መግቢያው አጠገብ ደገፍ ብሎ የቆመው ዮሴፍም ከእነርሱ የተሻለ ምስጢሩን የተረዳው አይመስልም።።

ግራ በመጋባት ከሚመለከቱት ሰዎች መካከል አንዱ ብቻ የሆነው ነገር የገባው ይመስላል።። ሽማግሌው ዘካርያስ - የደስታ እምባ ባቀረሩ ዓይኖቹ የሆነውን ሁሉ እያስተዋለ ራሱን ቀስ አደርጎ ነቀነቀ።። ከሰባት መቶ ዓመት በፊት የኖረው ነቢዩ ኢሳይያስ የተናገረው አንዳንድ ቃል ታወሰው።

”እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ... ” (ኢሳይያስ 7፥14) “ሕጻን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ... “ (ኢሳያስ 9፥6-7)

ዘካርያስ ይህን እያሰላሰለ በሃሳቡ ጭልጥ ብሎ ሄደ።። ነቢዩ ስለዚህ ሕጻን የተናገረው ትንቢት ይህ ብቻ እንዳልሆነም አስታወሰ።። ሌሊት ሲቆጥራቸው እንደሚያድረው ከዋክብት ትንቢቱ የጠለቀ ምስጢር እንዳለውም ተከሰተለት።። በሌላ ስፍራ ደግሞ ነቢዩ ስለዚህ ሕጻን እንደዚህ ብሏል።

“ ... በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ህመማችንንም ተሸክሟል ስለመተላለፋችንም ቆሰለ ስለበደላችንም ደቀቀ ...” (ኢሳይያስ 53)

አሃ! አሁን ሁሉ ነገር ለዘካርያስ በራለት፤ ምስጢር ተገለጠ።። ትንቢት ተፈጸመ።። መስዋዕት የሚለው ቃል ለዚህ ታላቅ ትንቢት ቁልፍ መሆኑ ለዘካርያስ ታየው።። ሕጻኑ ከመንገሡ በፊት የክህነትና የመስዋዕትነት ስራ እንደሚጠብቀው ተረዳ።። ዘካርያስ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ቀና አደረገ። እንግዳውን ኮከብ ለማየት ብቻ አልነበረም።። ከኮከቡ ባሻገር አርቆ ተመለከተ። ለብዙዎች ገና የተሰወረው የአባቱ የአብርሃም አምላክ ያዘጋጀው ይህ የደኅንነት ምሥጢር ከኮከቡ ምስጢር የረቀቀ፣ ሌሊት ከተገለጹት መላእክት በጣም የራቀ፣ ከምሥራቅ ጠቢባን ዕውቀት እጅግ የመጠቀ፣ ከሮማውያን ወታደሮች ኃይልም ብዙ ጊዜ የላቀ - ግን ሥጋ ለብሶ በመካከላቸው የተኛ ሕጻን መሆኑን አስተዋለ።። ለሌሎች ለማስረዳት ግን በጣም የተመሰቃቀለ መሆኑ እንደማይቀበሉት ተገነዘበ።። ምን ብሎ ያስረዳቸው? “ድንቅ መካር” እንዳይላቸው ምክር የማይገባቸው ዕምቢተኞች ስለሆኑ ደንታ እንደማይሰጣቸው ገመተ። “ኃያል አምላክ” እንዳይላቸው ከዕለት ኑሯቸውና ጥቅማቸው አሻግረው የማይመለከቱ ቅርብ አሳቢዎች ናቸው።። “የሰላም አለቃ” እንዳይላቸው ሰላምን እንደ ተረት ብቻ በወሬ የሚያውቁ ስለሆኑ እንቆቅልሽ እንደሚሆንባቸው አወቀ።። የሚናገረው ቢጠፋው፥
“የሰማነውን ነገር ማን አምኖአል?” ብሎ በጥያቄ ተወው- እርሱም እንደነቢዩ ኢሳይያስ።።

“ግሩም ድንቅ ነው ያንተ ስራ
ግሩም ድንቅ ነው ያንተ ስራ”